የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

፳ኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 29
ADDIS ABABA 25th March, 2014


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፬/፪ሺ፮ ዓ.ም**


የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ.......................................................ገጽ ፯ሺ፫፻፵፱


**አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፬/፪ሺ፮**

## ስለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የወጣ አዋጅ

በቆዳ ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት ላይ ከፍተኛ ተጽኖ የሚያሳድረው በሥራ ላይ ያለው ኋላቀር፣ የተንዛዛ እና ከፍተኛ የግብይት ወጪ የሚያስከትለው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓትን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በከፍተኛ ደረጃ የሚታየውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ብክነትን እና የጥራት ጉድለትን ለማስቀረት የሚያስችል የግብይት ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት በጥራት ደረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የምርቱ አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ አከመቻቸትና አጓጓዝ ሂደትን የሚያሻሽሉ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በሥራ ላይ በነበረው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት አዋጅ ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት የግብይት ሥርዓቱን ዘመናዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፬/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**CONTENTS**

**Proclamation No. 814/2013**


**Raw Hides and Skins Marketing Proclamation ....... ........................................................ Page 7349**


**PROCLAMATION No. 814/2013**

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR RAW HIDES AND SKINS MARKETING

WHEREAS, it has become necessary to improve the existing backward, inefficient and cost ineffective market structure of raw hide and skin which creates negative impact on the competitiveness of the leather industry;

WHEREAS, it has become necessary to establish raw hide and skin market structure that could avoid the existing raw hide and skin wastages and quality defects;

WHEREAS, it has become necessary to put in place an improved system of raw hide and skin collection, processing, storage and transportation to conduct the marketing of raw hides and skins on the basis of quality standards;

WHEREAS, it has become necessary to fill the gaps identified in the existing Raw Hides and Skins Marketing System Proclamation to modernize the market structure;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE

### GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Raw Hides and Skins Marketing Proclamation No. 814/2013".


ያንዱ ዋጋ
Unit price 9.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ “ጥሬ ቆዳ” ማለት ከበሬ፣ ከላም፣ ከወይፈን፣ ከጊደር፣ ከግመል እና ከመሰል እንስሳ የሚገኝ ትኩስ፣ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ቆዳ ነው፤

፪/ “ጥሬ ሌጦ” ማለት ከበግ፣ ከፍየል፣ ከጥጃ፣ ከአዞ፣ ከጥንቸል፣ ከሰጎን፣ ከዓሳ እና ከመሳሰሉት የሚገኝ ትኩስ፣ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሌጦ ነው፤

፫/ “ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦ” ማለት እንስሳው ከታረደ ከስድስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከላት የቀረበና በጨው ያልተዘጋጀ ወይም በአየር ያልደረቀ እርጥብ ቆዳ ወይም ሌጦ ነው፤

፬/ “ጨው” ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማዘጋጀት የሚያገለግል ኬሚካል ጨው ብሎ የሰየመው ጨው ነው፤

፭/ “የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን የመሰብሰብ፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝ፣ የማከማቸት፣ የመሸጥና የመግዛት ሂደት ነው፤

፮/ “የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት” ማለት አግባብ ባለው አካል በተሰየሙ የግብይት ማዕከላት ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚፈጸምበት ሂደት ነው፤

፯/ “ሁለተኛ ደረጃ ግብይት” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች፣ የኤክስፖርትና ከፍተኛ ቄራዎች እና ገዢ በሆኑ ቆዳ ፋብሪካዎች መካከል በሚደረግ ውል አማካኝነት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚፈጸምበት ሂደት ነው፤

፰/ “የግብይት ተሳታፊ” ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚሳተፉ አምራቾችን፣ አቅራቢዎችን፣ ባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎችን እና የቆዳ ፋብሪካዎችን ያካትታል፤

፱/ “አምራች” ማለት አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ቄራ፣ የኤክስፖርት ቄራ ወይም ለግል ፍጆታ የእንስሳት እርድ የሚፈጽም ወይም በእርድ አገልግሎት ላይ በመሰማራት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ “raw hide” means fresh, air-dried or salt treated hide obtained from ox, cow, steer, heifer, camel or such other animal;

2/ “raw skin” means a fresh, air-dried or salt treated skin obtained from sheep, goat, calf, crocodile, rabbit, ostrich, fish or such other similar animals;

3/ “fresh hide or skin” means a fresh hide or skin not treated with salt or dried by air and supplied to hide and skin market center in not more than six hours after the animal slaughtered;

4/ “salt” means a salt designated as chemical salt by the Ethiopian Standards Agency for the treatment of raw hide and skin;

5/ “raw hide and skin marketing” means the process of collecting, processing, transporting, storing, selling and buying of raw hide and skin;

6/ “first level marketing” means a marketing process in which the marketing of raw hides and skins is conducted in accordance with this Proclamation at market centers designated by the appropriate organ;

7/ “second level marketing” means a marketing process in which the marketing of raw hides and skins is performed in accordance with this Proclamation by a contract entered in to between, suppliers, export abattoir and big abattoir as seller, and tanneries as buyer;

8/ “market actor” includes producers, suppliers, traditional hides and skins processors and tanneries participating in hides and skins marketing;

9/ “producer” means small or big abattoir, export abattoir or person slaughtering animals for household consumption or engages in providing slaughtering service and supplies raw hides and skins to market;

፲/ “አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ቄራ” ማለት አግባብ ባለው አካል አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ተብሎ የተሰየመ ቄራ ነው፤

፲፩/ “የኤክስፖርት ቄራ” ማለት የቁም እንስሳትን በማረድ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን የሚያዘጋጅና የሚያቀነባብር ድርጅት ነው፤

፲፪/ “አቅራቢ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል ገዝቶ ለቆዳ ፋብሪካ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

፲፫/ “የቆዳ ፋብሪካ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን በማልፋት፣ በማለስለስና በማዘጋጀት ወደ አለቀ ቆዳ ምርት ደረጃ የሚያደርስ ፋብሪካ ነው፤

፲፬/ “ባህላዊ ቆዳ አልፊ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን በባህላዊ መንገድ በማልፋት ባህላዊ የቆዳ ቁሳቁሶች የሚያመርት ሰው ነው፤

፲፭/ “ማጓጓዣ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማጓጓዝ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ሲሆን የጭነት እንስሳንም ያጠቃልላል፤

፲፮/ “የማጓጓዝ ፈቃድ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከቄራ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል ወደ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም ወደ ቆዳ ፋብሪካ ለማጓጓዝ እንዲቻል አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፲፯/ “አሳሳች ድርጊት” ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሂደት ውስጥ የግብይት ተሳታፊዎችን ወይም የመንግሥት አካልን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማንኛውም ድርጊት ነው፤

፲፰/ “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊነት ንግድ ለመሰማራት የሚያስችሉ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰኑ መስፈርቶችን አሟልቶ ለተገኘ ሰው በሚመለከተው የሴክተር መሥሪያ ቤት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፲፱/ “ሚኒስቴር” ማለት የንግድ ሚኒስቴር ነው፤

፳/ “አግባብ ያለው አካል” ማለት እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የንግድ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

10/ “small or big abattoir” means an abattoir designated as small or big by the appropriate organ;

11/ “export abattoir” means an enterprise engaged in slaughtering of live animals and processing of meat and meat products for export market;

12/ “supplier” means a person who buys raw hides and skins from first level raw hides and skins market center and supplies them to tanneries;

13/ “tannery” means a factory curing and tanning raw hides and skins to finished leather;

14/ “traditional tanner” means any person who processes raw hide and skin in traditional manner and produces traditional leather goods;

15/ “means of transportation” means a vehicle used for transportation of raw hides and skins and includes pack animal;

16/ “transporting permit” means a permit issued by the appropriate organ to transport raw hides and skins from an abattoir or first level market center to a storage and processing warehouse or to a tannery;

17/ “misleading act” means any act misleading or deceiving market actors or government body in the marketing process of raw hides and skins;

18/ “certificate of competence” means a certificate issued by the relevant sectoral government institution to a person who fulfills the requirements to engage in the business of marketing of raw hides and skins stipulated pursuant to the relevant provisions of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686//2010;

19/ “Ministry” means the Ministry of Trade;

20/ “appropriate organ” means, as the case may be, the Ministry or a regional organ authorized to issue business license;

፳፩/ "ሴክተር መስሪያ ቤት" ማለት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓቱን በማስፈፀምና በመደገፍ ሂደት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ትስስር ያላቸውን የፌደራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት የሚያጠቃልል ነው፤

፳፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፳፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በአገሪቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ላይ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት

## ፬. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ወይም አንቀጽ ፮ መሠረት በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ግብይት ይሆናል።

## ፭. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት

፩/ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚፈጸምባቸው የገበያ ማዕከላት አደረጃጀት እና አስተዳደር ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

፪/ በግብይት ማዕከላት ውስጥ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚካሄደው:-

ሀ) በግለሰብ አምራቾች እና በአቅራቢዎች፤

ለ) በግለሰብ አምራቾች እና በባህላዊ ቆዳ አልፊዎች፤ ወይም

ሐ) በአነስተኛ ቄራዎች እና በአቅራቢዎች፤

መካከል ይሆናል።

21/ "sectoral government institution" includes the federal and regional executive bodies that have direct or indirect relationship in implementing and supporting raw hide and skin marketing system;

22/ "region" means any state referred to under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

23/ "person" means any natural or juridical person;

24/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to any person directly or indirectly involving in raw hides and skins marketing within the country.

## PART TWO

## RAW HIDES AND SKINS MARKET STRUCTURE

## 4. Raw Hide and Skin Marketing

The marketing of raw hides and skins shall be carried out at first or second level marketing in accordance with Article 5 or Article 6 of this Proclamation.

## 5. First Level Marketing of Raw Hides and Skins

1/ The organization and administration of market centers where first level marketing of raw hides and skins to be conducted shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

2/ The first level marketing of raw hides and skins at market centers shall be conducted between:

a) individual producers and suppliers;

b) individual producers and traditional tanners; or

c) small abattoirs and suppliers.

፫/ በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ሊሆን ይችላል።

፬/ ለመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚቀርበው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ትኩስ ወይም በአየር የደረቀ ብቻ ይሆናል።

፭/ በአቅራቢ የሚፈጸም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዢ በአቅራቢው በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት መፈፀም አለበት።

፮/ በአቅራቢ የተገዛው ጥሬ ቆዳና ሌጦ የማጓጓዣ ፈቃድ ወጥቶለት ወደ አቅራቢው ወይም በባህላዊ አልፊው የማዘጋጃና የማከማቻ መጋዘን ይሸኛል።

፯/ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዋጋ በጥራት ደረጃ ይወሰናል።

፰/ ከአምራች በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም ሰው በቆዳና ሌጦ ንግድ ለመሰማራት የሚያስችል የፀና የንግድ ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

## ፮. <u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት</u>

፩/ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት የሚፈጸመው፦

ሀ) በአቅራቢዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፤

ለ) በከፍተኛ ቄራዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፤ ወይም

ሐ) በኤክስፖርት ቄራዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፤

መካከል ይሆናል።

፪/ በሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከል የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ሊሆን ይችላል።

፫/ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት የሚፈጸምበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ትኩስ፣ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል።

፬/ በሁለተኛ ደረጃ ግብይት የግብይቱ ውል በፅሁፍ መሆን ያለበት ሆኖ የውሉ ዝርዝር ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተመለከቱትን መያዝ አለበት።

3/ The marketing of raw hides and skins at the first level marketing may be conducted by dealings or auction.

4/ Raw hides and skins to be supplied for first level marketing shall only be fresh or air-dried.

5/ Purchasing of raw hides and skins by a supplier shall be conducted only by himself or his agent.

6/ Raw hides and skins bought by a supplier shall be transferred to the processing and storage warehouse of the supplier or the traditional tanner accompanied with transporting permit.

7/ The price of raw hides and skins shall be determined by their quality.

8/ Any person, other than producer, participating in first level marketing of raw hides and skins shall have a valid business license to engage in the business of raw hides and skins.

## 6. <u>Second Level Marketing of Raw Hides and Skins</u>

1/ The second level marketing of raw hides and skins shall be conducted between:

a) suppliers and tanneries;

b) big abattoirs and tanneries; or

c) export abattoirs and tanneries.

2/ The marketing of raw hides and skins at the second level marketing may be conducted by dealings or auction.

3/ Raw hides and skins to be supplied for second level marketing may be fresh, air-dried or salt treated.

4/ The sale contract in the second level marketing shall be in written form and contain the particulars specified by the directive to be issued by the Ministry.